፫ ፤ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ አውሬውን ፡ በይዞታቸው ፡ሥር ፡ ካላደረጉ ፡ በስተቀር ፡ የግል ፡ ነዋሪዎች ፡ የአውሬውን ፡ ሀብትነት ፡ ሊያገኙ ፡ አይችሉም ።

መዝጊያ ፤

በዚሁ ፡ ጽሑፍ ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ የሰጠነው ፡ የማስጠንቀቂያ ፡ ቃል ፡ መጠኑ ፡ የጽሑፉ ፡ ደራሲ ፡ ከገመተው ፡ በላይ ፡ ይጋንን ፡ ይሆናል ፡ ተራ ፤ ሰዎች ፡ ሳይመራመሩ ፡ ማጠቃለያ ፡ ሊሰጡ ፡ ይችላሉ ፤ ሰጥተዋልም ፤ ግን ፡ ለእነዚህ ፡ ማጠቃለያዎች ፡ የሚመሩት ፡ ትንተናዎች ፡ ብዙ ፡ ሲሆኑ ፡ አጥጋቢ ፡ የሆኑት ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። የአንቀጽ ፡ ፲፴ ፡ ሊሰጠው ፡ የተፈለገው ፡ «ትርጉም ፡ በእርግጥ ፡ ሊታወቅ ፡ አይችልም ፡ ይሆናል ። በእውነቱ ፡ አንቀጽ ፡ በታወጀበት ፡ ጊዜ ፡ በጠቅላላው ፡ ተቀባይነት ፡ ያለው ፡ ትርጉም ፡ መኖሩን ፡ ለመጠራጠር ፡ በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ አሉ ። ነገር ፡ ግን ፤ በየትም ፡ አገር ፡ እንደሚደረገው ፡ በኢትዮጵያም ፡ በሕገ ፡ መንግሥትና ፡ በተራ ፡ ሕግ ፡ የአተረጓጐም ፡ ዘዴዎች ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ እንዲኖር ፡ ያስፈልጋል ። ስለዚህ ፡ «የምንተረጉመው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡» አንቀጹ ፡ ምን ፡ እንዲፈጸም ፡ የታሰበ ፡ መሆኑን ፡ መመርመር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በተግባር ፡ እንዲውልና ፡ ከአዲስ ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ እንዲስማማ ፡ ማድረግ ፡ አለብን ።